
# ቱኒዝያ ግብጽና ዛሬ ሊቢያ የደረሰው የቋያ እሳት ሰደድና

# በቅጥረኝነት የተነሳው ስማችን !

**ነቢዩ ሲራክ- ከሳውዲ አረቢያ**

## ሰሞነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳዎች . . .

እለተ አርብ አመሻሹ ላይ በአንድ የጓደኞች እድርና በኮሚኒቲው ካፍቴሪያ በተደረገ ማህበራዊ ግልጋሎት ስብሰባ ከተለያዩ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቸ ጋር የመገናኘት እድል አግኝቸ ነበር፡፡ ከወትሮው በተለየ ሞቅ ያለ ክርክርና ውይይት ያስነሱ ሁለት ጉዳዮች ተከስተዋልና ውይይቱ ቀጠለ፡፡ የተነሱት ጉዳዮች አንዱ በጅዳና አካባቢዋ ኮሚኒቲ ባሳለፍነው ሃሙስ በጠራው አጠቃላይ ስብሰባ የቀረበው የተፋለሰ የፋይናንስ ሪፖርትና በሪፖርቱ የቀረበው ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ኪሳራ ጉዳይ ሲሆን ሌላውና ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ በሊቢያው አመጽ ከተነሳ ከጥቂት ቀናት ወዲህ የኢትዮጵያውያን ዜጎች ፓስፖርት በሊቢያ ቅጥረኛ ሆነው እንደተገኙ አስመስሎ የቀረበው ቀልብ የሚስብ ዜና ነበር፡፡ ከ15 አመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ ወገንተኛነት ያልታየባቸው አዲስ አምባሳደር መጡ በተባለ ማግስት የኮሚኒቲው ኪሳራ አነጋጋሪ የሆነው የህዝብ ንብረት ጉዳይ ተሸፋፍኖ እንዳያልፍ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ማዘዛቸው እሰየው ነው ተባለ፡፡ ከዚህ ባለፈ ኮሚኒቲው ከኪሳራ ትርምስ ሊላቀቅ ያልቻለበት ሚስጥር ስላማይታወቅ ከማዘን ባለፈ ብዙ ለማለት ጊዜው አይደለምና ሰሞነኛ መነጋገሪያ ወደ ሆነው ወደ ሊቢያ የኢትዮጵያውያን ጉዳይ አመራ ዘንድ እገደዳለሁ፡፡ ይህ ጉዳይ ለሁሉም በኢትዮጵያዊነታችን ዙሪያ የመጣ መከራ በመሆኑ እያነሳን ብንጥለውም " ቅጥረኝነት ሊሆን አይችልም !" ከሚል ባለፈ በመካከላችን እንደ በፊቱ ልዩነት አለመታየቱ ከሁሉም በላይ አስደስቶኛል ! ወሬው በአልጀዚራና በአልአረቢያ በተነገረ ቅጽበት በኢትዮጵያ ውያኑ ድህረ ገጾች የተገኘውን መረጃ አረብኛው በእንግሊዝኛ ተተርጉመው መቅረቡም መልካም ነው፡፡ ለሚቀርቡት መረጃዎች የማውቀውን ለማለትና በዚህ ዙሪያ መልስ ቢጤ ለመስጠት ከጀልኩና ከጊዜ ጋር አልገጥምልህ አለኝ፡፡ ከሁሉም በላይ የቀረበውም መረጃ ስላላጠገበኝ መልስ እያሻው ዝምታን መምረጤ ግን አልተመቸኝም ፡፡



በአልጀዚራ የቀረበው የኢትዮጵያውያን ፓስፖርት



ቅጥረኞች የተባሉ አፍሪካውያን በእስር ላይ

የሳውዲ አረቢያ ንጉስ አብደላ ቢን አብድልአዚዝ ከሦስት ወራ ህክምና በኋላ በሰላም ወደ ሳውዲ መመለሳ ቸውን አስመልክቶ ከዜጎች እንዲከፋፈል በንጉሱ ከተበረከተው 36 ቢሊዮን ዶላር ስጦታ ጋር በርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለአንድ ቀን እረፍት በመስጠት ስራ ዘግተዋል፡፡ እኔ የምሰራበት ኩባንያ ግን ስራ አልተዘጋም፡፡ ምሽቱን እንዲያ ከመብተክተክ አልፌ በተከታታይ የማቀርባቸውን መጣጥፎች ለማዘገጃጀት ብሞክርም አልተቻለኝም ! የጀመርኩትን ሳልጨርስ በተጋደምኩበት እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ ! . . . ስራ የገባሁት አረፋፍጀ ነበር፡፡ ቢሮ እንደገባሁ አንድ ሳውዲ አረቢያ ውስጥ ተወልዶ ያደገ ፍልስጥኤማዊ አረብ የስራ ባልደረባየ ከማለዳ ሰላምታው ቀጥሎ ያቀረበልኝ የሚረብሽ ጥያቄ ነበር፡፡ ወዳጀ ዜናው ግራ አጋብቶት ያሳሰበው የነበረውን ሁሉ አውጥቶ የሃበሾችን ከእስራኤል ወታደሮች ጋር መዝመትና ዛሬም በሊቢያ ቅጥረኞች ስለተባልንበት ዜና ጠየቀኝ፡፡ ማዘኔ አልቀረም! ስሜቴን ደብቄ መመልስ ነበርብኝና ለመልሱ ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም፡፡ በእስራኤል ያሉት የሃበሻ ዝርያ ያለባቸው ቤተ እስራኤሎች በፍልስጥኤምና በእስራኤል ውጊያ መሳተፋቸውን አንስቶ የሰማውንና ያየውን ጠየቀኝ፡፡ ጥያቄውን በጥያቄ እመልስለት ገባሁ. . .ጠቅላይ ሚኒስትር ናታንያሁም ሆኑ መከላከያ ሚኒስትር ይሁድ ባራክ በእስራኤል ምድር አለመወለዳቸውንና የመጡበትን ሃገር ጠቀስኩለት! አዎንታውን አገኘሁ. . . ቀጠልኩና እንደዚያ ሁሉ ያያቸው ሃበሾች ኢትዮጵያ የተወለዱና ያደጉ በዘር ግን እስራኤላዊ መሆናቸውን ገለጽኩለት፡፡ ያም በመሆኑ ትግላቸውን የሚያካሂዱት በኢትዮጵያውነታቸው ሳይሆን እስራኤላዊ በመሆናቸው ለሃገራቸው እየተዋደቁ ስለመሆኑ መልስ ምሳሌ ጭምር ሰጠሁትና ተግባባን ! በሊቢያ ተገኙ ስለተባሉ ቅጥረኞችም ከዚህ በታች በዘረዘርኳቸው መሰረተ ሃሳቦች ሳልወጣ ለማስረዳት ሞከርኩ፡፡ ተስማማን !



በውጊያ ላይ ተገደለ የተባለ አፍሪካዊ ሬሳ

የቀረኝ ቀድሞውኑ መልስ ልሰጥበት ፈልጌ ወዳልተሳካልኝ መድረክ ይህችን ማታወሻ ማቅርብ ነበርና በጥድፊያም ቢሆን የሚመስለኝንና የሚገባኝን ያህል ላጋራችሁ ነብሴ አስገድዳኛለችና እነሆ . . .

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click "print", select the "Broadgun pdfMachine printer" and that's it! Get yours now!

## "ሽብርተኞች. . . ቦዘኔዎች. . . ጸረ ህዝቦች !" የአምባገነኖች መልስ . . .


የቀድሞው የቲኒዝያ መሪ ቢን አሊ

ዝምታውና ዘገምተኘነቱ "ያልረባ ትውልድ" ያስባለው የኛ ዘመን ወጣት በቱኒዝያ በግብጽና በሊቢያ በአንባገነኖች ላይ ባነሳው ሰላማዊ አመጻ አለም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እየቀየረው ይገኛል፡፡ ትናንት በቱኒዝያው ቢን አሊ የአመጹ ማዕበል ሲያንገዳግዳቸው "ጥቂት የመንገድ ላይ ቦዘኔዎች " ነበር ያሏቸው . . .እኒያን ጀግኖች ! አመጹ እንደ ሰደድ የቋያ እሳት ባስገራሚ ፍጥነት እየተቀጣጠለ ግብጽ በደረሰ ማግስት ፕሬዚደንት ሙባረክም ተመሳሳይ የንቀት መልስ ሰጡ! በታህሪር አደባባይ የተሰበሰቡ ትንታግ ወጣት ግብጻውያንን "በጥቂት ጸረ ዲሞክራሲ ሃይላት በጽንፈኞች የሚታገዙ..." አሏቸው ! ሁኔታው ግን የጽንፈኞች የቦዘኔዎችም ሆነ የጸረ ዲሞክራሲ ሃይላት አልነበረም ! ሃቁን መዋጥ እየመረራቸው በመጣበት ሰአት " ስልጣንዎትን ይልቀቁ ! አንፈልግዎትም ይውጡ !" የሚለውን የህዝብ አመጽ ሲበረታ ባደረጉት ንግግር " እህት ወንድሞቸ . . .እኔ የዚህች ሃገር የቁርጥ ልጅ ነኝ እንጅ የግብጽ ጠላት አይደለሁም. . .የምሞተውም በግብጽ ምድር ነው !" ብለው አረፉ ! ሃገራቸውን ለቀው እንደማይወጡ መሸነፍ መንበርከካቸውን ለመሸፋፈን በመቃጣት የተማጽ ኖ ኑዛዜ በሚመስል ንግግራቸው አስታወቁ ! አረቦች ብስጭት ምሬት ንቀታቸውን የሚገልጹትን የመጨረሻ መንገድ ግብጾች ተጠቀሙ . . . በሙባረክ ትዕቢት የተቆጡ ነዋሪዎች ሳይመካከሩ ባንድነት ጫማቸውን እያወለቁ ወደ ሙባረክ ምስል እየወረወሩ ጠፈጠፉት ! ይህ በሆነ በማግስቱ ሁስኒ ሙባረክ በውርደት ስልጣናቸውን ለቀቁ !


የቀድሞው የግብጽ መሪ ሁስኒ


ግብጻውያን በሙባረክ

## የሊቢያ ፍዳ . . .

የአመጽ ቋያው እሳት ሊቢያን መለብለብ ያዘ. . .ቱኒዝ በአመጽ ስትናጥ " ቢን አሊ እድሜ ልኩን ቢገዛ ችግሩ ምንድነው?" አያሉ ለፕሬዚደንቱ ድጋፍ የሰጡትና በህዝብ አመጽና የለውጥ ጥያቄ ሲያሚርቱ በነበሩት አምባገነን መሪ ኮሎኔል ጋዳፊ ቤትም አመጽ ሰተት ብሎ ገባ ! ብሶት የወለደው የህዝብ አመጽ ነውና ወጠምሻ የጋዳፊ ቅልብ ልጃገረድ ኮማንዶ አንጋቾቻቸው ቀርቶ የረቀቀ የጦር ሃይልና ለ42 አመታት በምድረ ሊቢያ የተደራጀው አፋኝ ሃይል አመጹን ሊገታው አልቻለም ! ጋዳፊ በተለመደ ዘራፍ አፋቸው አመጻውንና ያብጠለጥሉት ገቡ "... የአልቃኢዳ አሸባሪዎችና ሊቢያን መልሰው በቅኝ አገዛዝ መቆጣጠር የሚፈልጉ የውጭ ቅጥረኞች ስራ ነው. . ." ማለት ያዙ!የአልጀዚራ ቴሌቭዥንን በመደገፍ የካጣርን መንግ ስት አጥብቀው ሲዎቅሱ የአረቡ አለም መገናኛ ብዙሃንን በሊቢያ ሁከት እንዲፈጠር ምክንያት መሆናቸውን በምሬት ተናግረዋል. . . አረቦችን ጣሊያን እንግሊዝ አሜሪካኖችን ውሻ እያሉ ከመሳደብ አለፉም !ቀጠሉና ሰላማዊውን ተቃውሞ "በአሸባሪዎች እጅ የተሰበ ኩ ቦዘኔዎች በአደንዛዥ እጽ ተገፋፍተው ሊቢያን ሊያፈርሱ አይጠ መጎጦች ናቸው . . ." ያሏቸው ! ጋዳፊን የሚወዱ ማናቸውም ሊቢያውያን በአውራ መንገድ ወጥተው ይፋለሙ ዘንድ የጅምላ ጭፍጨፋ ጥሪ ነጋሪታቸውን ሲጎስሙ አረንጓዴው ህገ መንግስታቸውን ለእርምጃቸው ቅዱስነት መረጃቸው መሆኑን ዋቢ በማድረግ ነበር ! ጋዳፊ ከአንድ ሰአት በላይ ባደረጉት ንግግራቸው የአሜሪካ ጦር በኢራቅ ፈሉጃ የአልቃኢዳን ቅጥረኞች ለመደምሰስ የወሰደውን የአየር ጥቃት እያመሳሰሉ ከቢንጋዚን፤ የአዛውያን፤ የአልቤዳን የቶብሩክንና የቀሩትን በህዝቡ የተያዙ ከተሞችን "አሸባሪዎች" ከሚሏቸው ለማጽዳት ከራሳቸው "የካጣጥፋ" ጎሳ አባላት የተገነባውን አየር ሃይል እንደሚጠቀሙ በተለመደው ንቀት በተቀላቀለበት ድንፋታቸው ለአለም አሳወቁ ! እ.ጎ.አ በ1986 የሚሏቸው የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ሮናልድ ሬገን "ያበደ ውሻ" ያሏቸው ኮሎኔል ጋዳፊን ከቀዩ መስመር ሲያልፉ በተምዘግዛጊ ጀቶች በደበደቧቸው ቤተ መንግስት ፍርስራሽ ህንጻ ሆነው ንግግር ሲያደርጉ እንደቀድሞው አሁን የከዳቸውን የሊቢያ ነጻነት ናፋቂ ህዝብ ለመሸበብ ነበር፡፡ እንደቀድሞው "ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ወረራ እንከላከል!" በሚል በዎናው ፍርስራሽ ያሰሙት ንግግር መጨበጫ የሌለው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የአብዮቱ ታጋይ እንጂ መሪ አይደለሁም እስከማለትና የነዳጅ ሃብቱ የናንተ ነው ድርሻችሁን የመካፈል ሃቅ


pdfMachine
A pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click "print", select the "Broadgun pdfMachine printer" and that's it! Get yours now!

አላችሁ አሉ ጋዳፊ ፤ ሊቢያንን ሃገራችሁንና መሪያችሁን ከውጭ ወራሪና ከአሸባሪዎች ለመጠበቅ አደባባይ ውጡ አሉ ጋዳፊ. . . ሴት ወንድ፤ ትልቅ ትንሽ፤ ህጻን አዛውንትና ፍቅረኞች ሳትቀሩ ተያይዛችሁ ሊቢያን አድኑ አሉ ጋዳፊ. . . ባለቀ ሰአት ! በሊቢያ ከሚገኙት ጎሳዎች መካከል የታላቁ ጎሳዎች ወርፈላና የቀሩት ጎሳዎች የኮሎኔል ጋዳፊን አስተዳደር እንደ ማይፈልጉት አስታውቀዋል:: ራሳቸውን ከጋዳፊ ነጻ ያደረጉ ግዛቶች ንግግራቸውን ሳይጨርሱ በንቀት ጫማቸው እያወለቁ በቴሌብዥን የሚተላለፈውን ምስላቸውንና ንግግራቸው እየጠፈጠፉ እደጋዳፊ ጸያፍ ቃላትን ሳይጠቀሙ " ኢንታ ከዛብ !" አሏቸው ! በአረብናው አንተ ውሸታም ማለታቸውን ነው በንዴት ! እ.ጎ.አ በ1986 በአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖች ድብደባ የሴት ልጃቸው ደም ከፈሰሰበት ቦታ ላይ ሆነው ያደረጉትን ንግግር እንዳበቁ የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጀኔራል አብድልፈታህ የኑስና የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዋና ሃላፊ ስራቸውን ለቀቁ. . . በተለያዩ አለማት የሚገኙ የሊቢያ መንግስት ዲፕሎማቶች "ጋዳፊ በጅምላ ዘር ማጥፋት እርምጃቸውን አወጁ !" ሲሉ




በመቃወም ስራቸውን መልቀቅ ያዙ. . . የመንግስታቱ ድርጅት የአረብ ሊግና የአፍሪካ ህብረት ከመብተክተክ ያለፈ ውሳኔ ላይ መድረስ አልቻሉም. . .ከትናንቱ የርዋንዳ የጅምላ ዘር ማጥፋት እልቂት አልተማርንምና በጨካኙ መሪና በልጆቻቸው በአደባባይ አዋጅ ነግረው በህዝብ ላይ ክንዳቸውን ሲያሳዩ ጉልበተኞችን ማስቆም አልቻልንም ! የመንግስታቱ ድርጅት ፤ ምዕራባውያን፤ አሜሪካ፤ አረብ ሊግና አፍሪካ ህብረት ሊቢያውያንን ለመታደግና ትልቁን ቦታ መጫዎት ቢገባቸውም ዳር ሆነው ግፍ ሲፈጸም በዝምታ መመልከትን መርጠዋል ! አሜሪካኖች የኮሎኔል ጋዳፊንና የአራት ልጆቻቸውን ንብረቶች ማገዳቸውና የአውሮፓ ህብረት ጀርመን፤ ፈረንሳይና እንግሊዝ ተመሳሳይ የንብረት እገዳን ጨምሮ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ገደብ ለማድረግ መስማማታቸው የተሻለ እርምጃ ነው ቢባልም እስካሁን ባለው ሂደት ከ2000 ሁለት ሽህ በላይ ነዋሪዎች እንደሞቱ በሚነገርበት ሰአት ጊዜ ሲሄድ ሰቆቃው ሳይበዛ ደም መፋሰሱ እንዲያቆም አንድ ሊሉ ይገባል ! ሊብያውያን እያለቀሱ የድረሱልን ጥያቄ በሚያቀርቡበት በዚህ ሰአት የተባበሩት መንግስ ታት አባል ሃገራት ዛሬም እንደሳምንቱ ሁሉ በመሰብሰብና ከመምከር አልበ ዘኑም . . . ለእርምጃ ዘግይተው በአደባባይ እየተካሄደ ያለውን የሊቢያውያንን ጭፍጨፋ ነገ ተጨባጭ የተቡዳደሰ በድን መረጃ እያቀረቡ እንባና ሳግ እየተናነቃቸው በተለመደው ይቅርታ እንደ ሩዋንዳው እልቂት ሆዳችን እንዳያባቡት እሰጋለሁ ! ጋዳፊን አጋሮቻቸው (በህይወት ከተረፉ ማለቴ ነው)የፍጥኝ አስረው በፍርድ ቤት ቢያቀርቧቸው ትርጉም የሌለው ከመሆን ያለፈ አይሆንምና ግድያው እንዲያቆም አለም ባንድ ሊያብር ይገባል !



## መከረኛው ስማችን . . .

የኑሮ ውድነት አስመርሯቸው በሊቢያ በኩል ወደ አውሮፓ ሃገራት ለመሄድ ብለው በተለያዩ የሊቢያ ከተሞች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ከዘብጥ አልፎ በአደባባይ እየተወነጀሉና እየተገደሉ መሆኑን ሰምቻለሁ:: እውነታውን ግን ማረጋገጫ መንገድ የለም:: ረብሻው እንደ ተጀመረ ይህንን የገለጸልኝ ቢንጋዚ ስልክ ደውየ ያነጋገርኩት ወንድምም ከትናንት በስቲያ በሊቢያውያን ነዋሪዎች ቤት ለቤት በሚደረግ ፍተሻ "ቅጥረኛ" ተብሎ እየተደበደበ መወሰዱ በዚያው ስልክ ደውየ ያገኘኋት ሌላ ስደተኛ እህት እየተንሰቀሰቀች ገልጻልኛለች ! ዛሬ ደግሞ ስልኩ አይሰራም. . . ተዘግቷል ! የአረብ መገናኛ ብዙሃን ኢትዮጵያውያን ቅጥረኞች ከጋዳፊ ጎን መሰለፋቸውን ለማስረዳት ፓስፖርታቸውን በቴሌቭዥናቸው አሳይተዋል ! መገናኛ ብዙሃን ስራቸው መረጃ ማቀበል ነውና የተባለውን ውንጀላ በማቅረባቸው ላይ ችግር የለብኝም :: የሆነው "ከብት ባልዋለበት ኩብት ለቀማ" ነውና ውንጀላውን አምነን ለመቀበል በቂ የሆነ መረጃ ልናገኝ ይገባል :: በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ባህሪ ምንም ይሁን ምን ዜጎቹን ለኮሎኔል ጋዳፊ ቅጥረኛነት አሳልፎ ይሰጣል ብላችሁ ማመን ቀርቶ አታስቡ ማለት ባይቻለኝም የሰማነውን ከማመናችንና ከመናገራችን በፊት ልናስተውለው ይገባል ለማለት እወዳለሁ ! ይህን የምላችሁ ወሬ ለማድመቅ አይደለም:: ገና ሁከቱ ሲጀመርና አንድ የሊቢያ አብራሪ በአፍሪካና የአየር መንገድ በኩል በተደረጉ ተደጋጋሚ በረራዎች በርካታ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አፍሪካውያን ለውጊያ እስከ 2000$ (ሁለት ሽህ ዶላር) እየተከፈላቸው ትሪፖሊና ቢንጋዚ አየር ጣቢያዎች ማመላለሱን ይፋ ባደረጉ ማግስት ሁኔታውን ለማጣራት ሞክሬ ነበር:: ወደ ተለያዩ ሊቢያ ከተሞች ስልክ በመደወል ያገኘኋቸውን ወንድሞችና እህቶች ስላለው ሁኔታ አጫውተውኛል ". . . ኢትዮጵያውያን በዚህ ጭፍጨፋ ተቀጣሪ አጥቂ ሳይሆን ፤ተፈላጊ ተጠቂ ነን ! " በማለት እየደረሰባቸው ያለውን ሽብርና መከራ በተዘጋው ቤታቸው ድምጻቸው እንዳይወጣ እየታገሉ ገልጸውልኛል:: የጋዳፊ መንግስት አረመኔያዊ ስርአት ለመሆኑ የሚያውቁት 42 አመታት የተጨቆኑት ሊብያውያን ብቻ አይደሉም !

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click "print", select the "Broadgun pdfMachine printer" and that's it! Get yours now!

ከሞት የተረፉትና የሊቢያን በርሃና የአረመኔ ጸጥታ አስከባሪዎችን ቆመጥ አልፈው የባህሩን መከራ ገፈት ቀምሰው በአሜሪካ ፤በካናዳና በአውሮፓ የሚገኙ የዛሬ ብጹአን ኢትዮጵያውያን ሊነግሩን ይገባል ! እኔም በዚያ ያሉ ሃበሾችን ጉዳይ እድሉን አግኝቸው ማየት ባልችልም የሚገፉት የመከራ ህይወትና ታሪካቸው ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ በስልክ በኢሜልና በተለያዩ መንገዶች የማገኛቸው መረጃዎች የወገኖቻችን የህይወት ምስቅልቅሉን ፍንትው አድርገው በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ባንድ ወቅት ወደ አውሮፓ ለመሄድ ሲሉ በረሃ ላይ በሊቢያ ጸጥታ አስከባሪዎች የተያዙ ኢትዮጵያውያን ወህኒ ከወረዱ በኋላ በማደንዘዣ ራሳቸውን እንዲስቱ ተደርጎ ሃኪም ቤት ተወስደው ጎናቸው በሰላ ቢላዋ እየተቀረደደ ኩላሊታቸው አልተወሰደምን ?ይህ እኮ በሊቢያ እስር ቤቶች በኛ ዜጎች ላይ ተከስቷል ! ጊዜው ሩቅ ቢሆንም ይህ ሆኗልና ሊዘነጋ አይገባም ! በአለም አቀፍ ደረጃ ተደማጭነታቸው እየተስፋፋ ያሉት በአልጀዚራና በአል አረቢያ ያየነው የኢትዮጵያውያን ፓስፖርት ታሪክ በየቤቱ ታድነው የተለቀሙ አለያም በሃይል ተይዘው በጋዳፊ ወታደሮች ተገደው የታጠቁ ስደተኞች ሊሆኑ ይችላሉ እንጅ ለኮለኔል ጋዳፊ ድጋፍ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በተደረገ ድብቅም እንበለው ሌላ አይነት ግንኙነት ለተዋጊነት የመጡ ቅጥረኞች ሊሆኑ አይችሉም ! ታዋቂ መገናኛ ብዙሃን እያነሱ የሚጥሉት መረጃ ቀርቶ ሃላፊነት የሚሰማቸው ማናቸውም አለም አቀፍ እውቅና የሌላቸው መገናኛ ብዙሃን ለሚሰጧቸው መረጃዎች አክብሮት አለኝ፡፡ ተጠያቂነት ከሚሰማቸው ወገኖች የሚሰራጩ መረጃዎች እስከሆኑ ድረስ መረጃውን ከማሰራጨ ታቸው አስቀድሞ ለሚናገሩት ዜና



ምንጭና ባለቤት ስለመኖሩ ሙሉ እምነት አለኝ ፡፡ በአልጀዚራም ሆነ በቀሩት ጣቢያወች የቀረቡት ፓስፖርቶች የኢትዮጵያን አይደሉም ማለት አይቻልም፡፡ ካልረጋችውና በሁከት በመናጥ ላይ ካለችው ከሊቢያ የሚወጡ መረጃዎች አስተማማኝ ናቸው ማለት አይቻልምና በቅጥረኝነት የተሰማሩ ከተባሉት ኢትዮጵያውያንና ጉዳይ በቅርብ ማወቅ እስካልተቻለ ድረስ የሚነገረውን ለማመን ያስቸግራል፡፡ ቅጥረኛ ተብየዎችን የአቀጣጠር አመጣጣቸውን ሁኔታ ስንሰማ ብቻ ሃቁን እንደምንረዳ ጥርጥር የለኝም፡፡ ያ እስኪሆን ጉዳይ ለምን ተነሳ ባልልም እንደ አንድ ሃገር ዜጋ ሃቁን እስከንደርስበት መከረኛ ስማችን በዚህ እንዳይጎድፍ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ ይህን ስል ከዚህ በላይ ከጠቀስኳቸው ኢትዮጵያው ያን ምንጮችን መረጃዎችን በማጣቀስ ሲሆን በእርግጠኝነት ዜጎቻችን በቅጥረኝነት ተሰማርተዋል ብለን የምናምን ካለን የምናቀርበው መረጃ ሊኖር ይገባል! ይህን ማድረግ ካልቻልን ግን ዛሬ በቅጥረኝነት ስማችን ሲነሳ ፖለቲ ካ ልዩነት ሳይገድበን ወሬው በተሰራጨባቸው ቋንቋዎች ሁሉ ለአለም ህብረተሰብ መልስ ልንሰጥ ይገባል ! ከዚሁ ጎን ለጎን እንደ የኛ መንግስት እንደ ሃብታም ሃገራቱ አሜሪካና ምዕራባውያን አውሮፕላን ልኮ ዜጎቹን ይሰብስብ ለማለት አልቃጣም፡፡አቅሙ አይፈቅድምና ! ነገር ግን ድሃ አፍሪካ ሃገራት እንደሚያደርጉት ሊቢያን በሚያዋስኑ ሃገራት ያሉ ዲፕሎማቶች በድንበር እንዲዘልቁ በማድረግ ለዜጎቻችን እርዳታ ሊያደርጉ ላቸውና ከሁከት ሰቆቃው ለማውጣት ከፍተኛ የነብስ አድን ሙከራ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡የሃገራችን መልካም ገጽታ ለመገንባት መርሃ ግብር ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የሚገልጸው መንግስታችን በአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ስማችን እንዳይጎድፍ እንደቀሩት አፍሪካ ሃገራት ሁሉ በጉዳዩ ላይ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ዛሬ በሊቢያ ምድር እየሆነ ያለውን ለመገመት አይቻለን ምና ለተቸገሩት ሁሉ የጭንቁ አማላጅ እግዚአብሄር አምላክ ይድረስላቸው የሚለው እንደቀራችሁት የእኔም የዘወትር ጸሎት ነው !

ቸር ይግጠመን !

የካቲት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!